# ጊዜና ሂደት የአቋማችንን ትክክለኛነት እያረጋገጠ ነው!

## ለአባሎቻችንና ለደጋፊዎቻችን በሙሉ

ያለፉት ሁለት ዓመታት ለኢዴአፓ-መድህን እጅግ ከባድ የፈተና ዓመታት ሆነው አልፈዋል። በአንድ በኩል ፓርቲያችን ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለለት ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል የግንቦቱን ምርጫ ተከትሎ ወደ አንድ ወሳኝ ምዕራፍ ሊሸጋገር በተቃረበበት ወቅት ከተደቀኑበት አደጋዎች ለመታደግ ከፍተኛ ትግል አድርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ ከምርጫው በኋላ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የራሱን ሕልውና አደጋ ላይ በሚጥልና የሕዝቡን ምኞትና ተስፋ በሚያመክን መንገድ እንዳይሄድ ለማድረግ ከፍተኛ ትግል አድርጓል። ይህንን ተገቢ ትግል ማድረጋችን እንደ ክህደትና ጥፋት ተቆጥሮ ፈጽሞ ለፓርቲያችንና ለመሪዎቹ የማይገባ የስም ማጥፋትና የተቀነባበረ የአሉባልታ ዘመቻ ተካሂዶብናል። በዚያን ወቅት ፓርቲያችን የወሰደው አቋም ስህተት እንኳ ቢሆን ኖሮ ባለፉት ዓመታት ለትግሉ መጠናከርና መዳበር ወሳኙን ሚና ለተጫወተው ለኢዴአፓ-መድህን ይህ የከፋት ጥቃት በምንም መመዘኛ ቢሆን የሚገባው አልነበረም።

የግንቦቱ ምርጫ ላይ የማጭበርበር ድርጊት ስለመፈፀሙ ኢዴአፓ-መድህን አንዳች ጥርጣሬ አልነበረውም። በቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ውስጥ በተደረገው ክርክር ኢዴአፓ-መድህን ይህንን የተጭበረበረውን የምርጫ ውጤት በዝምታ ተቀብለን እንለፈውም አላለም። ይህ ከፍተኛ ስህተት ሊሆን መቻሉ ግልፅ ነበር። የወቅቱ የኢዴአፓ-መድህን አቋም በምርጫው ሂደት ተቃዋሚዎች ያገኙትን ከፍተኛ ውጤት በእጅ ውስጥ አስገብተን የበለጠ ተከታታይ ትግል በማድረግ በኢሕአዴግ ላይ ጫና መፍጠር ይቻላል የሚል ነበር። ቅንጅቱ የምርጫውን ውጤት አልቀበልም ብሎ ምን ሊያደርግ እንደሚችልና ምን ማድረግ እንዳለበት አስቀድሞ የተቀመጠ አቅጣጫና የተሰላ መንገድ አልነበረም። የቅንጅት ውስጣዊ ሁኔታና ድርጅታዊ ብቃት ለዚህ የተዘጋጀ አልነበረም። በተለይም የቅንጅቱ አመራር ውስጣዊ ሁኔታ በውጭ ሕዝቡ ከሚያይበት እውነታ በፍጹም የተለየ ሆኖ አመራሩ በጥቃቅን የስትራቴጂ ጥያቄዎች ጭምር መስማማት ተስኖት ውስጡ የትርምስ መድረክ ሆኖ በሚገኝበት ሁኔታ ቅንጅቱ ከራሱ ውስጣዊ ፍላጐትና ብቃት ውጪ ምርጫው ስለተጭበረበረ ብቻ በሕዝቡ ውስጥ በተፈጠረው ቁጣና ግፊት ተገፋፍቶ በኢሕአዴግ ላይ በ"ሕዝባዊ ትግል" ጫና ለመፍጠር መሞከሩ በኢዴአፓ-መድህን አስተሳሰብ አደገኛ የሆነ የስህተት አቅጣጫ ነበር።

የወቅቱን ሂደት ኢዴአፓ-መድህን እንደገመገመው ቅንጅት የምርጫው ውጤት ተጭበርብሯል በሚል ያነሳውን ጥያቄ እና ሕዝቡም ይህንን እንዲቃወም ያቀረበውን ጥሪ ተጠቅመው፤ ከቅንጅቱ አቅምና ችሎታ በላይ ሕዝቡን አነሳስተው፤ በቅንጅቱ ስም ሥልጣንን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩበትን አጋጣሚ ለመፍጠር ያሰቡ ኃይሎች የቅንጅቱን አጀንዳ ነጥቀውት ነበር። በቅንጅቱ ውስጥ የነበሩ አንዳንድ ሰዎችም ለእነዚህ ኃይሎች ራሳቸውን በመሣሪያነት ማዘጋጀታቸውንና የሥልጣን ሽግግርም የሚፈጠር ከሆነ በቂ ድርሻ ለማግኘት መደራደር መጀመራቸውን ኢዴአፓ-መድህን ተገንዝቦ ነበር። በዚህ ምክኒያት ነበር ኢዴአፓ-መድህን ቅንጅቱን ከዚህ የጥፋት መንገድ ለመመለስ የታገለው። ቅንጅቱ ከአቅሙና ችሎታው ውጪ ሌላው ቀርቶ ራሱን በራሱ ማቆም ባልቻለበት ሁኔታ ሥልጣንን በጉልበት ነጥቆ አገርን እመራለሁ ማለት የማይቻል ብቻ ሳይሆን ቢቻል እንኳን ክስተቱ ለአገሪቱ የሌላ ጥፋት መጀመሪያ እንደሚሆን ኢዴአፓ-መድህን አስረግጦ ተከራክሯል። በዚህ መንገድ መሄድ ከቅንጅቱ መሠረታዊ የፖለቲካ መርህና ዓላማ ውጭ መሆኑን ሊያሳምንም ሞክሯል።

ነገር ግን ይህ በቅንጅቱ ተቀባይነት አጣ። ተቀባይነት ማጣት ብቻ ሳይሆን ይህ የፓርቲያችን አቋም እንደ ጥፋትና ክህደት ተቆጠረ። ቅንጅቱ ኢሕአዴግን በአስቸኳይ በማስወገድ ሥልጣንን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር የሚያደርገውን መምዘግዘግ ለማደናቀፍ ሆን ተብሎ የተፈጠረ አስተሳሰብ ነው ተባለ። በመሆኑም ለጊዜውም ቢሆን ቅንጅቱን የተቆጣጠሩ ኃይሎች ይህንን የኢዴአፓ-መድህንን አስተሳሰብ ዋነኛ አራማጅ የሆኑ መሪዎችን ከሕዝብና ከትግሉ ሙሉ በሙሉ በመነጠል የፓርቲያችንን ድርጅታዊ ሕልውና ለማክሰም መጠነ ሰፊ ዕቅድ ዘረጉ። በአንድ በኩል ለትግሉ ጥንካሬ በሚል ሰበብ የተጣደፈ የውህደት እንቅስቃሴ በመጀመር በዚህ ሂደት ሆን ተብሎ የተቀነባበሩ ጥቃቶችን በፓርቲያችን ላይ በመፈፀም ይህንን ለመከላከል ተብሎ የሚደረጉ እርምጃዎችን ሁሉ ኢዴአፓ-መድህን ቅንጅቱን ለማፍረስ የሚያደረጋቸው አስመስሎ በመቀስቀስ ሕዝቡ ፓርቲያችንን እንዲያወግዝ ለማድረግ የሚያስችል ዘመቻ ተከፈተ። የቅንጅቱን አጀንዳ ከነጠቁና የሕዝቡንም ትግል ከጠለፉ ኃይሎችም አንዳንዶቹ ከዚህ ሴራ በስተጀርባ ሆነው ቀደም ሲል ጀምረው የኢትዮጵያ ተቃውሞ ትግል በኢዴአፓ-መድህን ማዕከልነት



☏ 0115-508727 0114655765 ✉ 101458
0115-508728

ፍልውሃ ቅርንጫፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር A/C 145